# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች



# ኢያሱ
# ኃላፊነትን
# ተቀበለ፡፡

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia



አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org



©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ሙሴ ሞቷል፤ ኢያሱ ደግሞ እስራኤላዊያንን እንዲመራቸው በእግዚአብሔር መመረጡን አውቋል፡፡ ኢያሱ ሠራዊቱን ከማዘጋጀቱ አስቀድሞ ፣ ራሱን ማዘጋጀት ነበረበት፡፡ ሕዝቡ ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል የሚታዘዙ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለኢያሱ በተስፋይቱ ምድር ድልንና ርስትን ሁሉ ሊሰጠው ቃል ገብቶለታል፡፡





እስራኤላዊያኑም
ለኢያሱ ለመታዘዝና
የእግዚአብሔርን ቃል
ለማክበር ቃል
ገብተዋል፡፡ ጥበብ
በተሞላበት መልኩ፣
አዲሱ መሪ የኢያሪኮን
ታላቅ ከተማ ለማጥናት
፣ ሰላዮችን ወደከነዓን
ላካቸው፡፡ የእስራኤል
የመጀመሪያ ውጊያ
እዚያ ነው
የሚደረገው፡፡



በከተማ ውስጥ ሰላዮች እንዳሉ አንድ ሰው ለኢያሪኮ ንጉስ ነገረው፡፡ እርሱም ፣ እነዚያን ሰላዮች እንዲያገኟቸው ወታደሮችን ላከባቸው፡፡ ፍለጋውም ሰዎቹ ተደብቀው በነበረበት በረሃብ ቤት ተጀመረ፡፡ ወታደሮቹ የረሃብን በር በሐይል በረገዱት፡፡ ረሃብም በፍጥነት ሰዎቹን ደበቀቻቸው፡፡

ወታደሮቹ ቤቱን ለቀው ከሔዱ
በኋላ ፣ ረሃብም ገመድ ተጠቅማ
በጥንቃቄ ከከተማው ቅጥር
ውጪ ጣለቻቸው፡፡ ሰላዮቹን
ለምን ረዳቻቸው? ምክንያቱም
እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር
እንዳለ ታውቅ ነበረ፡፡
እግዚአብሔር ሕይወቷን
እንዲያተርፍላት ትፈልግ ነበረ፡፡
ሰላዮቹ የረሃብንና
የቤተሰቦቿዋን ሕይወት
ለማትረፍ ቃል ገቡላት፡፡



ኢያሪኮ ከመድረሳቸው አስቀድሞ ፣ እስራኤላዊያን የዮርዳኖስን ወንዝ አቋርጠው ወደ ተስፋይቱ ምድር ወደ ከነዓን መሄድ ነበረባቸው፡፡ ነገር ግን ፣ ምንም አይነት ድልድይ አልነበረም፡፡ ሕዝቡ እንዴት አድርጎ ይሻገራል?



ካህናቶቹ አስርቱን ትእዛዛት የያዘውን ታቦት በመሸከም፣ ሕዝቡንና ወታደሮቹን እንዲመሩ ብሎ እግዚአብሔር ለኢያሱ ነገረው፡፡ ልክ የካህናቱ እግር የወንዙን ጫፍ ሲረግጥ ፣ እግዚአብሔር ታአምራትን አደረገ፡፡ እግዚአብሔር በውኃው መሐከል ማለፊያ መንገድን አደረገ፡፡



ሕዝቡ ሁሉ በሰላም ከተሻገረ በኋላ ፣ አስራ ሁለት ትልልቅ ድንጋዮችን በወንዙ ላይ አደረጉ ፤ ሌሎች አስራ ሁለት ደግሞ በከንዓን ወንዝ ዳርቻ ላይ አስቀመጡ፡፡ እነዚህ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገላቸውን ልልጆቻቸው የሚተርኩበት የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል እና ፍቅሩን የሚገልጡ ማስተወሻዎች ናቸው፡፡





ኢያሪኮ ጠንካራና ትልልቅ ግንቦች ነበሯት። ኢያሱ ጥቃቱን ሲያቅድ፣ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ተዋግቶ እንደሚያሸንፍ ለአዲሱ የእስራኤል መሪ እንዲነግረው ከሰማይ የሰራዊቱን አዛዥ ላከለት።



እግዚአብሔር ኢያሱን እንዴት ኢያሪኮን ማጥቃት እንደሚችል ነገረው፡፡ ይሔ እጅግ እንግዳ የሆነ እቅድ ነው፡፡ የእግዚብሔር ሕዝብም ከተማይቱን ለስድስት ቀናት በቀን አንድ ጊዜ መዞር ነበረባቸው ፤ በሰናተኛው ቀን ደግሞ ሰባት ጊዜ እንዲዞሩት፡፡ ከዚያም ፣ ጥሩምባውን እንዲነፉት እና እንዲጮሁ ፣ የከተማይቱም ቅጥር መሬት ላይ ይወድቃል፡፡

ኢያሱና ሰራዊቱም እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ ፡፡
ምንአልባት በኢያሪኮ የሚኖር ሕዝብ በእነሱ እየሳቀ
ይሆናል፡፡ ነገር ግን፣ በሰባተኛው ቀን ከሰባተኛው ዙር በኋላ
፣ ካህናቱ ቀንደ መለከቱን ነፉት፡፡ ከዚያም ፣ ልክ
እግዚአብሔር እንደተናገረው ፣
ታላላቆቹ የኢያሪኮ ግንቦች ወደቁ፡፡








የረሃብ ቤት ብቻ ደህና ሆኖ ቀረ፡፡ ቀዩን
ገመድ መስኮቷ ላይ እንዳስቀመጠችው
ነበረ፡፡ በፍጥነትም ፣ የኢያሱ ሰዎች
ረሃብንና የእርሷን ቤተሰብ አተረፉ፡፡
ከዚያም ፣ እግዚአብሔር እንደተናገረው
፣ ኢያሪኮ ፈረሰች፡፡



ኢያሱም ፤ የኢያሪኮን ወርቅ ፤ ነሃስና
ሀብት ሁሉ ለእግዚአብሔር አግልግሎት
እንዲሆን አድርጎ ሰጠ፡፡ ከዚያም ይሄንን ከፉ
ከተማ ሊሰራ የሚነሳ ሰው የተረገመ እንዲሆን ተናገረ፡፡
ኢያሱ ኢያሪኮን እንዴት አድርጎ እንዳሸነፈ በፍጥነት
በከንዓን ያለ ሁሉ ሰማ፡፡ እግዚአብሔር ከሕዝቡጋ
እንዳለም አወቁ፡፡

ኢያሱ ኃላፊነትን ተቀበለ፡፡

**ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ**

ኢያሱ 1-6

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16